ኣርማ

***ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ***

# ***ነጋሪት ጋዜጣ ፌደራል***

*መበል ዒስራን ሸሞንተን ዓመት ቁፅሪ* 5

ኣዲስ ኣበባ፣ ጥሪ 06 2014 ዓ.ም

***ኣብ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ***

***ብሓለዋ ቤትምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ዝወፀ***

ትሕዝቶ

ኣዋጅ ቁፅሪ 1265/2021

***መመስረቲ ኮሚሽን ኢትዮጵያ ሃገራዊ ዘተ ኣዋጅ --- ገፅ* 13879**

**<u>ኣዋጅ ቁፅሪ 1265/2021</u>**

***<u>መመስረቲ ኮሚሽን ሃገራዊ ዘተ ኢትዮጵያ ኣዋጅ</u>***

ኣብ ኢትዮጵያ ዝርከቡ ዝተፈላለዩ ፖለቲካን መረሕቲ ሓሳብን፣መንጎ ክፍልታት ሕብረተሰብን ብጣዕሚ መሰረታዊ ዝኾኑ ሃገራዊ ጉዳያት ናይ ሓሳብ ፍልልይን ዘይምርድዳእን ንምፍታሕ ሰፊሕ ሃገራዊ ናይ ህዝቢ ምኽክራት ኣካታቲ ብዝኾነ መንገዲ ብምክያድ ሃገራዊ ምርድዳእ ምፍጣር ኣድላዪ ብምዃኑ፣

ብጣዕሚ መሰረታዊ ብዝኾኑ ሃገራዊ ጉዳያት ኣካታቲ ሃገራዊ ምኽክር ምክያድ ዝሓሸ ሃገራዊ ምርድዳእ ንምህናፅ፣ ብክይዲ ናይ ምትእምማንን ተቐራሪብካ ናይ ምስራሕን ባህሊ ንምጉልባትን፣ ዝሓሰሩ ማሕበራዊ ክብርታት ንምሕዳስን ጠቓሚ ብምዃኑ፣ ሃገራዊ ክይዲ ዘተ ንምስላጥ ዘኽእል ስርዓት ብሕጊ ምዝርጋሕ ኣድላዪ ኮይኑ ስለዝተረኸበ፣

ሃገራዊ ዝርርባት ተቀባልነትን ተኣማንነትን ዘለዎም ክኾኑ ካብ ዘኽእሎም ጉዳያት ሓደ ምኽክራት ዘመዓራርን ዝመርሖ ኣካል ብቅዓትን ገለልተኝነትን ብምኻኑ፣ ምኽክራት ብብቅዓትን ብገለልተኝነትን ንምምራሕብን ለምትሕብባርን ዝኽእል ሰፊሕ ተቀባልነት ዘለዎ ትካል ምምስራት ኣድላዪ ኮይኑ ስለዝተረኸበ፣

ብመሰረት ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ቅዋም ዓንቀፅ 55 (1) ከምዚ ዝስዕብ ተኣዊጁ ኣሎ፡፡

## ***<u>ክፍሊ ሓደ</u>***

## ***<u>ሓፈሻዊ ድንጋገታት</u>***

1. ***<u>ሓጺር ኣርእስቲ</u>***

እዚ ኣዋጅ “መመስረቲ ኮሚሽን ኢትዮጵያ ሃገራዊ ዘተ ኣዋጅ ቁፅሪ 1265/2021” ተባሂሉ ክጥቀስ ይከኣል፡፡

2. ***<u>ትርጓመ</u>***

ኣገባብ ቃሉ ካልእ ትርጉም ዝህቦ እንተዘይኮይኑ በዚ ኣዋጅ፡

1. “ቤት ምኽሪ ኮሚሽን” ማለት ኩሉ ናይ ሃገራዊ ዘተ ኮሚሽነራት ብኣባልነት ዝሓቁፈ ቤት ምኽሪ ኮሚሽን እዩ፡፡

2. “ኮሚሽነር” ማለት ብመሰረት እዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 12 ብኣፈ ጉባኤ ኣቅራብነት ብቤትምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ዝስየም ኮሚሽነር ኮሚሽን ሃገራዊ ዘተ እዩ፡፡

3. “ሃገራዊ ዘተ” ማለት በዚ ኣዋጅን ቤት ምኽሪ ኮሚሽነራት ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ዝፍለዩ ኣጀንዳታት ብዝተፈላለዩ ኣካላት ዝርርብ ክግበረሉም ናይቲ ኮሚሽን ቤት ምኽሪ ብፌደራልን ብክልላትን ዘመዓራርዮ ዝርርባት እዮም፡፡

4. “ክልል” ማለት ብመሰረት ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ቅዋም ዓንቀፅ 47 ዝቆመ ክልል ኮይኑ፣ ምምሕዳራት ከተማ ኣዲስ ኣበባን ድሬዳዋን ይሓውስ፡

5. “ኣዘራራቢ” ማለት ኣብ ፌደራልን ክልልን ዘካይድዎ ሃገራዊ ናይ ዘተ መድረኻት ንክምራሕ ብምኽሪ ቤት ኮሚሽነር ዝምደብ ዝኾነ ሰብ እዩ፡፡

6. “ሰብ” ማለት ናይ ተፈጥሮ ሰብ ወይ ብሕጊ ናይ ሰብነት መሰል ዝተዋህቦ ኣካል እዩ፡፡

7. ዝኾነ ንወዲ ተባዕታይ ጾታ ዝተደንገገ ናይ ደቂ ኣንስትዮ ጾታ ውን ይሓውስ፡፡

3. <u>**መትከላት ሃገራዊ ዘተ**</u>

1. ሃገራዊ ዘተን ሓፈሻዊ ናይቲ ኮሚሽን ስርሓትን ዝመርሓሉም መትከላት

   ሀ. ኣጠቓላልነት

   ለ. ግልፅነት

   ሐ. ተኣማንነት

   መ. ምክእኣልን ምክብባርን

   ሰ. ምኽንያታውነት

   ረ. ናይ ምኽሪ ሓሳብ ተግባራውነትን ዓውዲ ተኮርን

   ዘ. ገለልተኛ ኣምዓራራይነት፣

   ሸ. ናይ ኣጀንዳታት ጥልቀትን ግቡእነትን

   ቀ. ዲሞክራስን ልዕልነት ሕግን

   በ. ብሄራዊ ጥቕሚ

   ተ. ሃገራዊ ባህላዊ ፍልጠታትን ክብርታትን ምጥቓም

2. ቤት ምኽሪ ኮሚሽን ኣድለይቲ እዮም ብምባል ዝኣምነሎም መትከላት ብተወሳኺ ከጠቓልል ይኽእል፡፡

<u>ክፍሊ ክልተ</u>

ብዛዕባ ምምስራት ኮሚሽን ፣ ዕላማ፣ ኣወዳድባ፣ ተግባርን ሓላፍነታትን

4. <u>**ምስረታ**</u>

1) ኮሚሽን ሃገራዊ ምኽክር ኢትዮጵያ (ካብዚ ንደሓር “ኮሚሽን” እንዳተባህለ ዝፅዋዕ) ካብ ፖለቲካ ውግንና፣ ካብ ዝኾነ ናይ መንገስቲ ወይ ካልእ ኣካል ፅዕንቶ ናፃ ዝኾነ ርእሱ ዝኸኣለ ናይ ሕጊ

ሰብነት ዘለዎ ኣካል ኮይኑ በዚ ኣዋጅ ተጣይሹ ኣሎ።

2) ናይ ኮሚሽን ተፀዋዕነት ንቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ይኸውን።

5. **<u>ዋና ቤት ፅዮ</u>**

ናይቲ ኮሚሽን ዋና ቤት ፅዮ ኣብ ኣዲስ ኣበባ ኮይኑ ከከም ኣድላይነቱ ኣብ ካልኦት ክልላት ጨንፈር ቤት ፅሕፈታት ክህልዎ ይኽእል፡

6. **<u>ዕላማ እቲ ኮሚሽን</u>**

እቲ ኮሚሽን ዝስዕቡ መሰረታዊ ዕላማታት ይህልዎ፡

1. ኣብ ዝተፈላለዩ ክፍልታት ሕብረተሰብ መሰረታዊ ብዝኾነ ሃገራዊ ጉዳያት ንዝተፈጥሩ ፍልልያት ወሳኒ ምኽንያታትን ዝርርባት ዝካየደሎም ርእሰ ጉዳያትን ብምፍላይ ዘተ ክግበረሎም ምምችቻው
2. ዝካየዱ ሃገራዊ ዝርርባት ኣሳታፊ፣ ብቕዓት ብዘለዎን ገለልተኛ ብዝኾነ ኣካልን ዝምርሑ፣ ናይ ዘይምርድዳእ መልዓሊታት ብትኽክል ብዝድህሰስ ኣጀንዳ ዘተኮሩ፣ ግልፂ ብዝኾነ ናይ ኣሰራርሓ ስርዓት ዝምርሑን ናይ ዘተ ውፅኢታት ንምፍፃምን ዘኽእል ትልሚ ዘለዎም ክኾኑ ብምግባር ውፅኢታዊ ዝኾኑ ሃገራዊ ናይ ዘተ መስርሕ ተግባራዊ ምግባር፣
3. ዝካየዱ ሃራዊ ዝርርባት ብዝተፈላለዩ ክፋላት ሕብረተሰብን ኣብ መንጎ መንግስትን ህዝብን ዘሎ ርክባት ንምምሕያሽ፣ ምትእምማን ዝሰፈነሉን ሓድሽ ናይ ፖለቲካ ስርዓት ንምፍጣር ብዘኽእልን ኣገባብ ዝርርባት ክካየዱ ስርዓት ምዝርጋሕ፣
4. ካብ ዝርርባት ዝተረኽቡ ናይ መፍትሒ ምኽሪ ሓሳባት ኣብ ተግባር ክውዕሉ ድጋፍ ብምግባር ኣብ መንጎ ዜጋታትን ኣብ መንጎ መንግስትን ህዝብን ምትእምማን ዝሰፈነሉ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ኣብ ዓለም ለኸ ደረጃ ክህነፅ ምኽኣል።
5. ንዘመናት ክንከባለሉ ዝመፁ ውሽጣዊ ሽግራት ብዝርርብ ንምፍታሕ ዘኽእል ናይ ፖለቲካ ባህሊ ንምምዕባልን ንህንፀት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ምቹው ድልድል ምፍጣርን
6. እዋናዊ ፀገማት ዘላቒ ብዝኾነ መንገዲ ተፈቲሖም ዘተኣማምን ሰላም ዝረጋገፀሉ ድልድል ፖለቲካውን ማሕበራውን ምፍጣር
7. ንሃገራዊ ምርድዳእን ድልዱል ቅቡልነት ዘለዎ ሃገረ መንግስቲ ንምህናፅን ፅኑዕ መሰረት ምቕማጥ እዩም።

7. **<u>ናይቲ ኮሚሽን ኣወቓቕራ</u>**

እቲ ኮሚሽን፡-

1. ናይቲ ኮሚሽን ቤት ምኽሪ
2. ዋና ኮሚሽነር
3. ምክትል ዋና ኮሚሽነር
4. ቤት ፅሕፈት

5. ከከም ኣድላይነቱ ኮሚተታትን

6. ኣድላዪ.ሰራሕተኛታትን ይህልውዎ።

7. ንሃገራዊ ምርድዳእን ድልዱል ቅቡልነት ዘለዎ ሃገረ መንግስቲ ንምህናፅን ፅኑዕ መሰረት ምቅማጥ እዩም።

8. ዘመን ስራሕ ኮሚሽን

8. <u>ናይቲ ኮሚሽን ናይ ስራሕ ዘመን ሰለስተ ዓመት እዩ</u>

1. ኣድላዪ ኮይኑ እንተድኣተረኺቡ ናይቲ ኮሚሽን ናይ ስራሕ ዘመን ብቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ክናዋሕ ይኽእል።

2. ናይቲ ኮሚሽን ናይ ስራሕ ዘመን ዝቑፀር በዚ ኣዋጅ መሰረት ናይቲ ኮሚሽን ኮሚሽነራት ካብ ዝተሸሙሉ ግዜ ጀሚሩ እዩ።

9. <u>ናይቲ ኮሚሽን ተግባርን ሓላፍነትን</u>

እቲ ኮሚሽን ዝስዕቡ ተግባራትን ሓላፍነትን ይህልዎ፦

1. ዘተ ዘጣጥሑን ዘፈፅሙን ዝተፈላለዩ መፅናዕትታት ዝካየዱን ምኽሪ ሓሳብ ዘመንጭዉን ኮሚተታትን ናይ በዓል ሞያ ጉጅለታትን የጣይሽ።

2. ቅድሚ ሐዚ ብመንግስታዊ ኮነ ዘይመንግስታዊ ትካላት ዝተገብሩ ሃገራዊ ከይድታት ዘተን ዝተረኽቡ ውፅኢታትን የፅንዕ። ብቀፃሊ ንዘካይዶም ሃገራዊ ዝርርባት ብእታወታት ይጥቐም።

3. ብዝተፈላለዩ ናይ ፖለቲካን ናይ ሓሳብ መረሕትን፣ኣብ መንጎ ክፍልታት ሕብረተሰብን ኣብ ሃገራዊ ጉዳያት ዘሎ ፍልልያት ብመፅናዕቲ፣ ብህዝባዊ ዝርርባት ወይ ካልኦት ኣገባብ ዘለዎም መንገድታት ብምጥቓም ይፍለ።

4. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 3 መሰረት ብዝተገለፁ ሜላታት ዝፈለዮም ጉዳያት መሰረት ብምግባር ናይ ዘተ ኣጀንዳታት ይቐርፅ፣ ዘተ ክግበረሎም የመቻችው፣ ዝርርባትን ዘተን የሳልጥ

5. ካብ መላእ ሃገር ዝተፈላለዩ ክፍልታት ሕብረተሰብ ዝውክሉ ተሳተፍቲ ዝሳተፉሉ፣ ሃገራዊ ምርድዳእ ንምምፃእ ዘኽእሉ ዝተፈላለዩ ናይ ዘተ ኣኼባታት ብፌደራልን ብክልልን ደረጃ ክካየዱ የመቻችው።

6. ብሃገራዊ ናይ ዘተ ጌባኤ ዝሳተፉ ተሳተፍቲ ግልፂ ብዝኾነ ጠለባትን ናይ ኣሰራርሓ ስርዓትን መሰረት ይፈሊ፣ ብምኽክር ክሳተፉ ይገብር፣ እዚ ዝምልከት ዝርዝር መምርሒ የውፅእ።

7. ምኽክራት ብኮሚሽነራት ወይ ናይ ኮሚሽነራት ቤት ምኽሪ ብዝሰይሞም ኣዘራረብቲ ክምርሑ ይገብር፣ ብኣዘራራብነት ዝምድቦም ሰባት ብዝተኻእለ መጠን በዚ ሕጊ ዓንቀፅ 13 ዝተጠቐሱ ንኮሚሽነርነት ዝበቕዑ ጠለባት ዘማልኡ ምዃኖም የረጋግፅ፣

8. ብኪዶት ምኽክር ዝግበሩ ምኽክራት ቃለ ጉባኤ ዝሕዙ፣ ዝቀረቡ ምኽሪ ሓሳባት ዘጠናኽሩን ኣወሃሂዶም ንኮሚሽነራት ቤት ምኽሪ ዘቕርቡን ሰብሞያታት ይምድብ፣

9. ናይ ቤት ፅሕፈት ናይ ውሽጢ ኣሰራርሓ ስርዓት ናይ ምኽክር ኣጀንዳታት ወይ ኣርእስቲ ዝምረፀሉ ዝምልከት፣ ኣብ ሃገራዊ ዝርርባት ዝሳተፉ ኣካላት ዝፍለይሉ ስርዓት ንምዝርጋሕን

ተመሳሳሊ ተግባራትን ንምስላጥ ዘኽእሉ ውሽጣዊ ደንብን መምርሒታትን የውፅእ፣ ኣብ ስራሕ የውዕል፣

10. ናይ ሃገራዊ ምኽክር ጉባኤ ኣጀንዳታት፣ ክይድታት ምኽክራት፣ ብዘተ ዝተረኽቡ ምኽሪ ሓሳባትን ምኽሪ ሓሳባትን ኣብ ተግባር ክውዕልሉ ዘኽእሎም ስልቲ ዝገልፅ ሰነድ ብምድላው ንቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ንኣፈፃሚ ኣካልን ካልኦት ዝምልከቶም ናይ መንግስቲ ኣካላትን የቕርብ፣ ንህዝቢ ውን ይነግር

11. መንግስቲ ካብ ሃገራዊ ዝርርባት ዝርከቡ ምኽሪ ሓሳባት ኣብ ተግባር ንምውዓል ዘኽእል ጭቡጥ ዝኾነ ትልሚ ከዳሉ ኣድላዪ ሓገዝ ይገብር

12. ናይ ምኽሪ ሓሳባት ኣፈፃፅማ ንምክትታል ዘኽእል ስርዓት ይዝርግሕ

13. ዕላምኡ ንምፍፃም ዘድልዩ ካልኦት ተግባራት የካይድ፡፡

10. <u>ናይቲ ኮሚሽን ቤት ምኽሪ ኣኼባ</u>

1. እቲ ቤት ምኽሪ ኮሚሽን ብውሽጢ ኣሰራርሓ ደንቢ መሰረት ስሩዕ ኣኼባ የካይድ፣ ኮይኑ ግን ክከም ኣድላይነቱ በቲ ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፃውዒት ወይ ካብ መንጎ ኮሚሽነራተ ሓምሳ ትድመሮ ሓደ (50+1) ናይቲ ኮሚሽን ኮሚሽነራት ሕቶ ክቕርቡ ክለዉ ኣብ ዝኾነ ግዜ ህፁፅ ኣኼባ ክገብር ይኽእል፡፡

2. ካብ መንጎ ኮሚሽን ኮሚሽነራት ሓምሳ ትድመሮ ሓደ (50+1) እንተድኣተረኺቦም ምልኣተ-ጉባኤ ይኸውን፡፡

3. ናይቲ ኮሚሽን ውሳኔ ብቤት ምኽሪ ኮሚሽን ኣባላት ብስምምዕነት ይኸውን፣ እንተኾነ ግን ብስምምዕነት ንምውሳን ምርድዳእ እንተዘይተበፂሑ እቲ ውሳነ ብቤት ምኽሪ ኮሚሽን ዝተረኽቡ ኮሚሽነራት ብኣብዝሓ ድምፂ ይሓልፍ

4. ኣብ ውሳኔ ኣወሃህባ ኮሚሽን ድምፂ ማዕረ ንማዕረ እንተድኣተኸፊሉ ናይ ኣካቢ ድምፂ ወሳንነት ይህልዎ፡፡

5. ናይዚ ዓንቀፅ ድንጋገታት ዝተሓለዉ ኮይኖም ናይ ቤት ምኽሪ ኮሚሽን ናይ ባዕሉ ናይ ኣኼባ ስነ-ስርዓት መምርሒ ክውፅእ ይኽእል፡፡

## <u>ክፍሊ ሰለስተ</u>

## <u>ብዛዕባ ኮሚሽነራት</u>

11. <u>ብዛዕባ ኮሚሽነራት</u>

1. እቲ ኮሚሽን ዓሰርተ ሓደ (11) ኮሚሽነራት ይህልውዎ፣

2. ናይቲ ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነርን ካልኦት ኮሚሽነራትን ብቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ይስየሙ፣

3. ናይ ቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ናይ ሹመት ውሳኔ ዝወሃብ ዝቐረቡ ሕፁያት በዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 13 ዝተቀመጠ ጠለባት ዘማልኡ ምዃኖም ብምርግጋፅ ይኸውን፡፡

12. <u>ናይ ኮሚሽነራት ኣሰያይማ</u>

ናይ ኮሚሽነራት ኣሰያይማ በዚ ዝስዕብ ኣገባብ ይኸውን፡-

1. ናይ ቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ኣፈ ጉባኤ ቤት ፅሕፈት ሕፁይ ናይ ኮሚሽን ኣባላት፣ ካብ ህዝቢ፣ ፖለቲካ ትካላትን ካብ ሲቪል ማሕበራት ኮሚሽነር ክኾኑ ዝኽእል ውልቀሰባት ጥቆማ ይቕበል፡፡

2. በዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 13 ዝተቀመጡ ጠለባት መሰረት ካብ ዝተጠቆሙ ሰባት እንተውሓደ ዓሰርተ ኣርባዕተ ኮሚሽነር ክኾኑ ዝኽእሉ ሕፁያት ብምፍላይ ናይ ሕፁያት ዝርዝር ንህዝቢ ወግዓዊ ብምግባር፣ ንኣፈ ጉባኤ የቕርብ።

3. ዝዳሎ ናይ ሕፁያት ዝርዝር ናይ ጾታን ካልኦት ናይ ብዙሕነት መግለፂታትን ዘጠቓለለ ክኸውን ኣለዎ፣

4. ኣፈ ጉባኤ ምስ ተናሓናሒ ናይ ፖለቲካ ውድባት፣ ሲቪል ማሕበረሰብ ትካላት፣ ኣብያተ ሃይማኖት ጉባኤ ኣመራርሓን ተወከልትን ብዝቐረቡ ሕፁያት ምኽክር ይገብር።

5. ኣፈ ጉባኤ በዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (4) ዝተገለፀ ምኽክር ድሕሪ ምግባሩ ካብ ዝቐረቡ ሕፁያት ከከም ኣድላይነቱ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነርን ኮሚሽነርን ኮይኖም ከገልግሉ ዝኽእሉ ሕፁያት ብቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ክስየሙ የቕ።

## 13. ንኮሚሽነርነት ዘብቅዑ ጠለባት

ዝኾነ ይኹን ኮሚሽነር ኮይኑ ዝስየም ሰብ ዝስዕቡ ጠለባት ከማልእ ኣለዎ:-

1. ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ዝኾነ
2. ኩሉ ሃይማኖታት፣ ናይ ኢትዮጵያ ብሄራት፣ ብሄረሰባትንን ህዝብን ብማዕረ ዓይኒ ዘገልግል
3. ናይ ዝኾነ ይኹን ፖለቲካ ውድብ ኣባል ዘይኮነ
4. ንሃገራዊ ምርድዳእ ሉዑል ኣስተዋፅኦ ከበርክት ዝኽእል
5. ፅቡቕ ስነ ምግባርን ስብእናን ዘለዎ
6. ኣብ ቅድሚ ህዝቢ እምነት ዘለዎ
7. ብከቢድ በን ተኸሲሱ ናይ ጥፍኣተኛ ውሳነ ዘይተሓላለፈሉ
8. ናይ ኮሚሽን ስራሕ ብግቡእ ንምስራሕ ዘኽእል ዝተማልአ ብቕዓት ዘለዎ።
9. ምሉእ ግዚኡ ንኮሚሽን ስራሕ ንምወዓል ፍቓደኛ ዝኾነ

## 14. ናይ ኮሚሽነራት ደሞዝን ጥቕምን

ደሞዝን ጥቕምን ኮሚሽነራት ንመንግስቲ ልዑል ተሰየምቲ ብዝተፈቕደ ደሞዝን ጥቕምን ኣገባብ ይፍፀም።

## 15. ናይ ኮሚሽነራት መሰልን ግዴታን

1. ዝኾነ ይኹን ኮሚሽነር ዝስዕቡ መሰላት ይህልውዎ:-

ሀ. ዘይምኽሳስ መሰሉ ብቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ እንተዘይተላዒሉ ወይ ኢድ ብኢድ እንተዘይተታሒዙ ብኮሚሽርነት ኣብ ዘገልግለሉ ግዜ ብበን ዘይምኽሳስ መሰል ኣለዎ።

ለ. በቲ ኮሚሽን ቤት ምኽሪ ስራሕ ብናፅነት ናይ ምስታፍን ድምፂ ናይ ምሃብ

ሐ. ንስራሕ ኣድላይቲ ዝኾኑ ሰነዳትን ካልኦት ጠቐምቲ መረዳእታታትን ናይ ምርካብ ፣ምምልካት፣

መ. ናይቲ ኮሚሽን ቤት ምኽሪ ኣብ ዝውስነሉ ኣገባብ ናይ ኮሚቴ ስራሕትን ካልኦት ስራሕትን ናይ ምስታፍ።

2. ዝኾነ ይኹን ኮሚሽነር ዝስዕቡ ግዴታታት ይህልውዎ:-

ሀ. ናይቲ ኮሚሽን ተግባርን ሓላፍነትን ብግቡእ ኩነታት ምፍፃም፣

ለ. ምሉእ ግዚኡ ንኮሚሽን ስራሕ ናይ ምውዓል

ሐ. ግጭት ጥቕሚ ናይ ምውጋድ

መ. ብኪደት ስራሕ ዝረኸቦ ምስጢር ናይ ምሕላው

ሰ. ናይ ኮሚሽን ገለልተኛነት፣ ዕቡቕ ሽም፣ ክብሪ ካብ ዘትሕቱን ውፅኢታውነት ካብ ዝዕንቅፉ ተግባር ናይ ምቁጣብ

ረ. ካልኦት ናይቲ ኮሚሽን ስርዓትን ደንብታትን ምኽባር

## 16. <u>ኮሚሽነራት ካብ ሓላፍነቶም ዝለዓሉሉ ኩነታት</u>

1. ዝኾነ ይኹን ኮሚሽነር በዞም ዝስዕቡ ኩነታት ካብ ሓላፍነት ክለዓል ይኽእል፦

ሀ. ብምኽንያት ሕማም ስሩዕ ተግባሩ ክካይድ ብዘይምኽኣል

ለ. ግልፂ ዝኾነ ናይ ብቕዓት ምጉዳል እንተድኣተራእዩ

ሐ. ከቢድ ናይ ስነ-ምግባር ጉድለት እንተድኣተራእዩ

መ. ብዘይ እኹል ምኽንያት ንተኸታታሊ ዓሰርተ መዓልቲ ኣብ ስራሕ ቦትኡ እንተዘይተረኺቡ፣ ወይ

ሰ. በዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 13 ካብ ዝተጠቅሱ ጠለባት ኣብ ግዜ ሹመት ኮሚሽነር ዘየማልኦ ጠለባት ምህላዉ እንተድኣተረጋገፁ፡፡

2. በዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 መሰረት ኮሚሽነር ካብ ሓላፍነት ዝለዓል ዝኾነ ይኹን መረዳእታ ብዘለዎ ወገን ተሓታትነት ዝቀረበ ምልክታ ዘእምን እዩ ኢሉ እቲ ኣፈ ጉባኤ ተቀቢሉ ንቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ብዝሕልፎ ሕቶ ወይ ካብ ሓደ ሲሶ ዘይውሕዱ ኣባላት ቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ኣለዓዓልነት ወይ ካብ ሰለስተ ዘይውሕዱ ኮሚሽነራት ሕቶ መሰረት ናይ ቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ብዝሕልፎ ውሳኔ ይኸውን፡፡

## 17. <u>ሓላፍነት ብድሌት ምልቓቕ</u>

ዝኾነ ይኹን ሓላፍነቱ ብገዛእ ፍቓዱ ምልቓቕ ዝደሊ ኮሚሽር ናይ ክልተ ወርሒ ናይ ፅሑፍ ቅድመ መጠንቐቕታ ንቤት ምኽሪ ኮሚሽነራትን ንቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ኣፈ ጉባኤን ብምሃብ ክለቅቕ ይኽእል፡፡

## 18. <u>ብዛዕባ ካልእ መንግስታዊ ሓላፍነት</u>

በዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 16 መሰረት ካብ ሓላፍነት ዝተላዕለ ወይ ብዓንቀፅ 17 መሰረት ብገዛእ ፍቓዱ ካብ ሓላፍነት ዝለቐቐ ኮሚሽነር ንክልተ ዓመት ንካልእ መንግስታዊ ሓላፍነት ኣይሕፀን፡፡

## 19. <u>ብዛዕባ ኮሚሽነር ምትካእ</u>

1. በዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 16ን17ን መሰረት ኮሚሽነር ካብ ሓላፍነት ክለዓል ከሎ ወይ ክለቅቕ ከሎ ወይ ብምኽንያት ሞት ኣብዝተፈለየሉ በዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 12 መሰረት ንኣፈ ጉባኤ ካብ ዝተላኣኹሉ ናይ ሕፁያት ዝርዝር ብኮሚሽነርነት እንተዘይተሰይሞም ሕፁያት ተተካኢ ኮሚሽነር ኮይኑ ብቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ክሽወም ይገብር፡፡

2. ናይዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (1) ድንጋገ ዝተሓለወ ኮይኑ ካብ ሓላፍነት ዝተላዕለ ወይ ዝለቐቐ ወይ ብምኽንያት ሞት ዝተፈልየ ዋና ኮሚሽነር ወይ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ብዝኾነ ግዜ ካብ

ዝተሰየሙ ኮሚሽነራት ወይ ካብ ተሓላላዊ ሕፁይ ኮሚሽነራት ብምምራፅ ክስየም እቲ ኣፈ ጉባኤ ንቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ የቕርብ።

## ክፍሊ ኣርባዕተ

## ብዛዕባ ኮሚሽን ቤት ምኽሪ፣ ዋና ኮሚሽነርን ቤት ፅሕፈትን

### 20. ቤት ምኽሪ ኮሚሽን

ቤት ምኽሪ ኮሚሽን ኩሎም ኮሚሽነራት ብኣባልነት ዝሓቆፈ እዩ።

### 21. ተግባርን ሓላፍነትን ቤት ምኽሪ ኮሚሽን

ቤት ምኽሪ ኮሚሽን ዝስዕቡ ስልጣንን ተግባራትን ይህልውዎ፦

1. ናይ ህዝቢ ምኽክር ዝግበረሎም ኣጀንዳታት ብዝርዝር ብምፍታሽ ምኽክር ክግበረሎም ምውሳን
2. ብኮሚተታ ተዳልዮም ዝቐርቡን ብህዝባዊ ዝርርባት ዝተረኽቡ ምኽሪ ሓሳባትን ብዝርዝር ብምፍታሽን ብምጥንኻርን ንቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ንፈፃሚ ኣካልን ካልኦት ዝምልከቶም ናይ መንግስቲ ኣካላትን ክቐርብ ምፅዳቕ
3. ናይ ቤት ፅሕፈት ዓመታዊ ባጀትን ትልምን መርሚሩ ናይ ምፅዳቕ
4. ናይ ቤት ፅሕፈት ሓፈሻዊ ሪፖርት መርሚሩ ናይ ምፅዳቕ
5. ኣድላዪ ኮሚተታት ናይ ምጥያሽ
6. ኣብ ክልላት ናይ ቤት ፅሕፈት ጨንፈራት ቤት ፅሕፈት ክምስረት ናይ ምውሳን
7. ናይቲ ቤት ፅሕፈት ናይ ኦዲት ርኽበት መርሚሩ ናይ ምፅዳቕ
8. ናይቲ ቤት ምኽሪ ኮሚሽነርን ምክትል ዋና ኮሚሽነርን ብተመሳሳሊ ግዜ ኣብ ግዜ ስራሕ ንተኸታታሊ ዓሰርተ መዓልቲ እንተዘይተረኺቦም ኣብ መንጎ ኣባላት ግዝያዊ ኣካቢ ናይ ምምራፅ
9. ናይቲ ቤት ፅሕፈት መዋቅራዊ ውህደት ናይ ምፅዳቕ
10. ናይቲ ቤት ፅሕፈት ሓላፊ ሹመት ምፅዳቕ
11. ነቲ ኣዋጅ ንምፍፃም ዘድልዩ መምርሒታት ናይ ምውፃእ
12. ናይ ኮሚሽነራት ናይ ስነ ምግባር መምርሒ ናይ ምውፃእ
13. ናይቲ ቤት ፅሕፈት መተሓዳደሪ ደንቢ ናይ ምውፃእ

### 22. ተግባርን ሓላፍነትን ዋና ኮሚሽነር

ናይቲ ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ዝስዕቡ ተግባራትን ስልጣንን ይህልውዎ፦

1. ናይቲ ኮሚሽን ቤት ምኽሪ ብኣቦ ወንበርነት ይመርሕ
2. ጠቕላላ ናይ ኮሚሽን ስራሕ ናይ ምምራሕ

3. ናይቲ ኮሚሽን ቤት ምኽሪ ኣኼባ ኣጀንዳታት ናይ ምቕራብ

4. ከከም ኣድላይነቱ ህፁፅ ኣኼባ ናይ ምፅዋዕ

5. ናይቲ ቤት ፅሕፈት ሓፈሻዊ ስራሕ ናይ ምቁፅፃር

6. ነቲ ኮሚሽን ብምውካል ምስ ካልኦት ኣካላት ርክባት ናይ ምግባር

7. ንቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ፀብፃባት ናይ ምቕራብ

8. ሓላፊ ቤት ፅሕፈት ኮሚሽን ሕፁይ ንቤት ምኽሪ ኣቕሪቡ ናይ ምስያም

9. ናይቲ ኮሚሽን ሰራሕተኛታት ብፌደራል መንግስቲ ሰራሕተኛታ ሕጊ መሰረት ናይ ምቁፃርን ምምሕዳርን፣

10. ናይቲ ኮሚሽን ናይ ባጀት ሕቶ ምስ ገንዘብ ሚኒስተር ብምድላው ንቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ምቅራብ፤

11. ካልኦት ብቤት ምኽሪ ኮሚሽን ዝወሃብ ተግባራት ምክያድ፤

23. <u>ተግባርን ስልጣንን ምክትል ዋና ኮሚሽነር</u>

ናይቲ ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር ዝስዕቡ ተግባርን ስልጣንን ይህልውዎ፡-

1. ዋና ኮሚሽነር ኣብ ዘይህልወሉ ግዜ ተኪኡ ይሰርሕ፤

2. ብዋና ኮሚሽነር ዝወሃቡ ተግባራት ይፍፅም፡፡

24. <u>ብዛዕባ ቤት ፅሕፈት ኮሚሽን</u>

1. ቤት ፅሕፈት ኮሚሽን ኮሚሽነር ብዘይኮነ ሓላፊ ይምራሕ

2. ቤት ፅሕፈቱ ካልኦት ኣድላይቲ ሰራሕተኛታት ይህልውዎ

3. ቤት ፅሕፈቱ ተፀዋዕነቱ ንዋና ኮሚሽነር ይኸውን፡፡

4. ተግባርን ሓላፍነትን ቤት ፅሕፈት ኮሚሽን

25. **ቤት ፅሕፈት ኮሚሽን**

ዝስዕቡ ተግባራትን ስልጣንን ይህልዎ ፡-

1. ናይቲ ኮሚሽን ቤት ፅሕፈት ትካላዊ ኣወዳድባ ፈለዩ ንቤት ምኽሪ ኮሚሽን ኣቕሪቡ ናይ ምፅዳቕ

2. ንኮሚሽን ሓፈሻዊ ምምሕዳርን ፋይናንስን ግልጋሎት ናይ ምሃብ

3. ንኮሚሽን ተግባርን ሓላፍነትን ኣድላዩ ዝኾኑ እታወታትን ካልኦት ግልጋሎታትን ናይ ምቕራብ፤

4. ቃለ ጉባኤታት፣ ውሳኔታት፣ መዛግብቲ ሕሳብን ካልኦት ሓበሬታታትን ኮሚሽን ብዝግባእ ወዲቡ ናይ ምሓዝ፤

5. ባጀት ኮሚሽን  ብምድላው ዋና ኮሚሽነር ምሕጋዝን

6. ካልኦት ብቤት ምኽሪ ወይ ብዋና ኮሚሽነር ዝወሃቡ ተግባራት ምፍፃምን፡፡

26. <u>ተግባርን ሓላፍነትን ሓላፊ ቤት ፅሕፈት</u>

1. ናይቲ ቤት ፅሕፈት ሓላፊ ዝስዕቡ ተግባራትን ስልጣንን ይህልዎ፡-

ሀ. ናይቲ ቤት ፅሕፈት ቅርፃዊ ኣወዳድባ ፈልዩ ንቤት ምኽሪ ኮሚሽን ኣቕሪቡ ናይ ምፅዳቕ

ለ. ናይቲ ቤት ፅሕፈት ተግባራት ብዝምልከት ንዋና ኮሚሽነርን ንቤት ምኽሪ ኮሚሽነራትን ሪፖርት ናይ ምቕራብ፣

ሐ. ናይቲ ቤት ፅሕፈት ትልሚ ስራሕ ንቤት ምኽሪ ኮሚሽን ኣቕሪቡ ናይ ምፅዳቕን፤

መ. በዚ ኣዋጅ ንቤት ፅሕፈት ዝተዋሀቡ ተግባራትን ስልጣንን ብምምራሕ ናይ ምምሕዳርን

2. ሓላፊ ቤት ፅሕፈት ተፀዋዕነቱ ንኮሚሽን ዋና ኮሚሽር ይኸውን፡፡

## <u>ክፍሊ ሓሙሽተ</u>

## <u>ፍሉይ ድንጋገታት</u>

27. <u>ምንጪ ባጀት</u>

1. ናይቲ ኮሚሽን ባጀት ብመንግስቲ ዝምደብ ይኸውን

2. በዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (1) ዝተደንገገ ዝተሓለወ ኮይኑ ካብ ካልኦት ሕጋዊ ምንጭታት ምርካብ ይከኣል፡፡

3. መትከላት ምምሕዳር ፋይናንስ መንግስቲ መሰረት ብምግባር ብቤት ምኽሪ ኮሚሽን ብዝፀድቅ ደንቢ መሰረት እቲ ኮሚሽን ነቲ ባጀት ናይ ምምሕዳር ምሉእ ናፅነት ኣለዎ፡፡

28. <u>መዛግብቲ ሒሳብ</u>

1. እቲ ኮሚሽን ዝተማልኡን ትኽክለኛን ዝኾኑ መዛግብቲ ሕሳብ ይሕዝ፡፡

2. ናይቲ ኮሚሽን መዛግብቲ ሕሳብን ገንዘባዊ ሰነዳትን ብዋና ኦዲተር ወይ ባዕሉ ብዝሰይሞም ኦዲተራት በቢዓመቱ ይምርመሩ፡፡

29. <u>ደንብን መምርሒን ናይ ምውፃእ ስልጣን</u>

1. ቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ናይ ኮሚሽነራት፣ ናይቲ ኮሚሽን ሰራሕተኛታት፣ ኣዘራረብቲ፣ ኣብ ከይዲ ዝርርብ ዝሳተፉ ኣካላት ኵነታት ስነ ምግባር  ብዝምልከት ደንቢ ከውፅእ ይኽእል፡፡

2. ቤት ምኽሪ ኮሚሽነራት እዚ ኣዋጅን በዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (1) መሰረት ዝወፁ ደንብታት ንምፍፃም ዘድልዩ መምርሒታት ከውፅእ ይኽእል፡፡

30. <u>ብዛዕባ ሰነዳት ኮሚሽን</u>

1. እቲ ኮሚሽን ናይ ስራሕ ግዚኡ ምስ ኣብቀዐ በቲ ኮሚሽን ናይ ስራሕ ዘመን ብዝተኻየዱ ሃገራዊ ምኽክራት ዝተዳለዉ ሰነዳት፣ ዝተታሕዙ ቃለ-ጉባኤታትን ተመሳሰልቲ ሰነዳትን ተሓልዮም ክፀንሑ ንቤት ፅሕፈት ቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ፣ ንቤተ መዛግብቲ ኢትዮጵያን ግልጋሎት ቤተ መፃሕፍትን ናይ ምርካብ ሓላፍነት ኣለዎ።

2. ንቤተ መዛግብቲ ኢትዮጵያን ግልጋሎት ቤተ መፃሕፍትን ካብቲ ኮሚሽን ዝተቐበሎም ሰነዳት ብኣገባብ ወዲቡ ናይ ምቕማጥን ዝተፈላለየ ፅላማ ምርኣይን ምጥቃምን ንዝደልዩ ሰባት ምጥቓም ክኽእሉ ናይ ምምችቻውን ሓላፍነት ኣለዎ።

31. <u>ናይ ምትሕብባር ግዴታ</u>

ዝኾነ ይኹን እቲ ኮሚሽን በዚ ኣዋጅ ዝተወሃቦ ሓላፍነት ንምውፃእ ኣብ ዝግበር ምንቅስቃስ ንዝቐርብ ዝኾነ ይኹን ሕጋዊ ሕቶ ናይ ምትሕብባር ግዴታ ኣለዎ።

32. <u>ተፈፃምነት ዘይብሎም ሕግታት</u>

ምስዚ ኣዋጅ ዝቃረኑ ዝኾነ ይኹን ሕግታት በዚ ኣዋጅ ዝተሸፈኑ ጉዳያት ተፈፃምነት ኣይህልዎምን።

33. <u>እዚ ኣዋጅ ዝፀንዓሉ ግዜ</u>

እዚ ኣዋጅ ብቤት ምኽሪ ተወከልቲ ህዝቢ ካብ ዝፀደቀሉ ታሕሳስ 20/2014 ጀሚሩ ዝፀንዐ ይኸውን።

**ኣዲስ ኣበባ ጥሪ 5/2014**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**ፕሬዝደንት ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ**

በኢትዮጵያ በሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነት እና አለመግባባት የሚታይ በመሆኑ፤ ይህንን ልዩነት እና አለመግባባት ለመፍታት ሰፋፊ ሀገራዊ የሕዝብ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ በማካሄድ ሀገራዊ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አካታች ሀገራዊ ምክክሮችን ማካሄድ የተሻለ ሀገራዊ መግባባትን ለመገንባት፣ በሂደትም የመተማመንን እና ተቀራርቦ የመሥራት ባህልን ለማጎልበት፣ እንዲሁም የተሸረሸሩ ማህበራዊ እሴቶችን ለማደስ ጠቃሚ በመሆኑ፤ ሀገራዊ የምክክር ሂደትን ለማሳለጥ የሚያስችል ሥርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሀገራዊ ምክክሮች ተቀባይነት እና ተዓማኒነት ያላቸው እንዲሆኑ ከሚያስችላቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ምክክሮቹን የሚያመቻቸውና የሚመራው አካል ብቃትና ገለልተኝነት በመሆኑ፤ ምክክሮቹን በብቃትና በገለልተኝነት ለመምራትና ለማስተባበር የሚችል ሰፊ ቅቡልነት ያለው ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታዉጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፭/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"የኮሚሽኑ ምክር ቤት"** ማለት ሁሉንም የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነሮችን በአባልነት ያቀፈ የኮሚሽኑ ምክር ቤት ነው፤

፪/ **"ኮሚሽነር"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሰረት በአፈ ጉባዔዉ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾም የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ነዉ፤

፫/ **"ሀገራዊ ምክክር"** ማለት በዚህ አዋጅና የኮሚሽነሮች ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በሚለዩ አጀንዳዎች ላይ በተለያዩ አካላት ውይይት እንዲደረግባቸው የኮሚሽኑ ምክር ቤት በፌደራልና በክልሎች የሚያመቻቻቸው ውይይቶች ናቸው፤

፬/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን፤ የአዲስ አበባንና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፭/ **"አወያይ"** ማለት በፌደራልና በክልል የሚካሄዱ ሀገራዊ የምክክር መድረኮችን እንዲመራ በኮሚሽነሮች ምክር ቤት የሚመደብ ማንኛውም ሰው ነው፤

፮/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፯/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

**፫. የሀገራዊ ምክክሩ መርሆዎች**

፩/ ሀገራዊ ምክክሩ እና አጠቃላይ የኮሚሽኑ ሥራዎች የሚመራባቸው መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) አካታችነት፤

ለ) ግልፅነት፤

ሐ) ተዓማኒነት፤

መ) መቻቻል እና መከባበር፤

ሠ) ምክንያታዊነት፤

ረ) የምክረ ሃሳቦች ተግባራዊነት እና አውድ ተኮርነት፤

ሰ) ገለልተኛ አመቻችነት፤

ሸ) የአጀንዳዎች ጥልቀት እና አግባብነት፤

ቀ) ዲሞክራሲ እና የሕግ የበላይነት፤

በ) ብሔራዊ ጥቅም፤

ተ) ሀገራዊ ባህላዊ እውቀቶችንና እሴቶችን መጠቀም።

፪/ የኮሚሽኑ ምክር ቤት አስፈላጊ ናቸው በማለት የሚያምንባቸውን መርሆዎች በተጨማሪነት ሊያካትት ይችላል።

## ክፍል ሁለት

## ስለኮሚሽኑ መቋቋም፣ ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ተግባር እና ኃላፊነቶች

**፬. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ) ከፖለቲካ ወገንተኝነት፣ ከማንኛውም የመንግሥት ወይም ሌላ አካል ተጽዕኖ ነፃ የሆነ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ

አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል።

**፭. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ክልሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

**፮. <u>የኮሚሽኑ ዓላማ</u>**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት መሠረታዊ ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ለተፈጠሩ ልዩነቶች ወሳኝ ምክንያቶችን በመለየት እና ውይይቶቹ የሚካሄዱባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በመለየት ምክክር እንዲደረግባቸው ማመቻቸት፤

፪/ የሚካሄዱት ሀገራዊ ምክክሮች አካታች፣ ብቃት ባለውና ገለልተኛ በሆነ አካል የሚመሩ፣ የአለመግባባት መንስዔዎችን በትክክል በሚዳስስ አጀንዳ የሚያተኩሩ፣ ግልፅ በሆነ የአሠራር ሥርዓት የሚመሩ እና የምክክሮቹን ውጤቶች ለማስፈፀም የሚያስችል ዕቅድ ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ውጤታማ የሆኑ ሀገራዊ የምክክር ሂደት ተግባራዊ ማድረግ፤

፫/ የሚካሄዱት ሀገራዊ ምክክሮች በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እንዲሁም በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመን የሰፈነበትና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ ውይይቶቹ እንዲካሄዱ ሥርዓት መዘርጋት፤

፬/ ከምክክሮቹ የተገኙ የመፍትሔ ምክረ ሃሳቦች በሥራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ በማድረግ በዜጎች መካከል እንዲሁም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል መተማመን የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲገነባ ማስቻል፤

፭/ ለዘመናትሲንከባለሉ የመጡ ውስጣዊ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ባህል ለማዳበር እና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ምቹ መደላድል መፍጠር፤

፮/ ወቅታዊ ችግሮች ዘላቂ በሆነ መንገድ ተፈተው አስተማማኝ ሰላም የሚረጋገጥበትን የፖለቲካ እና የማኅበራዊ መደላድል ማመቻቸት፤

፯/ ለአገራዊ መግባባት እና ጠንካራ ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግሥት ለመገንባት ጽኑ መሠረት መጣል ናቸው።

**፯. <u>የኮሚሽኑ አደረጃጀት</u>**

ኮሚሽኑ፡-

፩/ የኮሚሽኑ ምክር ቤት፤

፪/ ዋና ኮሚሽነር፤

፫/ ምክትል ዋና ኮሚሽነር፤

፬/ ጽህፈት ቤት፤

፭/ እንደአስፈላጊነቱ ኮሚቴዎች፤ እና

፮/ አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

**፰. <u>የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን</u>**

፩/ የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን ሦስት (፫) ዓመት ነው።

፪/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን
በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊራዘም
ይችላል።

፫/ የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን የሚቆጠረው በዚህ አዋጅ መሠረት የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

**፱. <u>የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነቶች</u>**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ ምክክሮችን የሚያመቻቹና የሚያስፈጽሙ፣ የተለያዩ ጥናቶችን የሚያካሂዱ እና ምክረ ሃሳቦችን የሚያመነጩ ኮሚቴዎችን እና የባለሙያ ቡድኖችን ያቋቁማል፤

፪/ ከዚህ በፊት በመንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተደረጉ ሀገራዊ የምክክር ሂደቶችን እና የተገኙ ውጤቶችን ያጠናል፣ በቀጣይ ለሚያካሂዳቸው ሀገራዊ ውይይቶች በግብዓትነት ይጠቀማል፤

፫/ በተለያዩ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያሉትን ልዩነቶች በጥናት፣ በሕዝባዊ ውይይቶች ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መንገዶች በመጠቀም ይለያል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አቀጽ (፫) መሰረት በተገለፁት ዘዴዎች የለያቸውን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የምክክር አጀንዳዎችን ይቀርፃል፣ ምክክር እንዲደረግባቸው ያመቻቻል፣ ምክክሮችን እና ውይይቶችን ያሳልጣል፤

፭/ ከመላ ሀገሪቱ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እና አካላትን የሚወክሉ ተሳታፊዎች የሚሳተፉባቸው፣ ሀገራዊ መግባባት ለማምጣት የሚያስችሉ የተለያዩ የምክክር ስብሰባዎችን በፌደራል እና በክልሎች ደረጃ እንዲካሄዱ ያመቻቻል፤

፮/ በሀገራዊ የምክክር ጉባዔ ላይ የሚሳተፉ ተሳታፊዎችን ግልፅ በሆኑ መሥፈርቶች እና የአሠራር ሥርዓት መሠረት ይለያል፣ በምክክሮች ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል፤ ይህን የተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፤

፯/ ምክክሮቹ በኮሚሽነሮች ወይም የኮሚሽነሮች ምክር ቤት በሚሰይማቸው አወያዮች አማካኝነት እንዲመሩ ያደርጋል፤ በአወያይነት የሚመድባቸዉ ሰዎችም በተቻለ መጠን በዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፫ ላይ የተመለከቱትን ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤

፰/ በምክክር ሂደቶች የሚደረጉ ምክክሮችን ቃለ ጉባዔ የሚይዙ፣ የቀረቡ ምክረ ሃሳቦችን የሚያጠናቅሩ እና አደራጅተው ለኮሚሽነሮች
ምክር ቤት የሚያቀርቡ ባለሙያዎችን ይመድባል፤

፱/ የጽህፈት ቤቱን የውስጥ የአሠራር ሥርዓት፣ የምክክር አጀንዳዎች ወይም አርዕስት የሚመረጡበትን የሚመለከት፣ በሀገራዊ ውይይቶች ላይ የሚሳተፉ አካላት የሚለዩበትን ሥርዓት ለመዘርጋትና መሰል ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ ውስጠ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያወጣል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

፲/ የሀገራዊ ምክክር ጉባዔ አጀንዳዎችን፣ የምክክሮቹን ሂደት፣ በምክክሮቹ የተገኙ ምክረ ሃሳቦችን እንዲሁም ምክረ ሃሳቦቹ በተግባር ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሥልት የሚገልጽ ሰነድ በማዘጋጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለአስፈጻሚ አካሉ እና ሌሎች የሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ያቀርባል፤ ለሕዝብም ይፋ ያደርጋል፤

፲፩/ መንግሥት ከሀገራዊ ውይይቶች የሚገኙ ምክረ ሃሳቦችን በተግባር ላይ ለማዋል እንዲችል ግልፅ እና ተጨባጭ የሆነ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

፲፪/ የምክረ ሃሳቦቹን አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፫/ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**፲ <u>የኮሚሽኑ ምክር ቤት ስብሰባ</u>**

፩/ የኮሚሽኑ ምክር ቤት በውስጥ አሠራር ደንቡ መሠረት መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ጥሪ ወይም ከኮሚሽነሮቹ መካከል ሃምሳ ሲደመር አንድ (፶+፩) የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ጥያቄ ሲያቀርቡ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤

፪/ ከኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች መካከል ሃምሳ ሲደመር አንድ (፶+፩) ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤

፫/ የኮሚሽኑ ውሳኔ በኮሚሽኑ ምክር ቤት አባላት በስምምነት ይሆናል፤ ሆኖም ግን በስምምነት ለመወሰን መግባባት ላይ ካልተደረሰ ውሳኔው በኮሚሽኑ ምክር ቤት ላይ በተገኙ ኮሚሽነሮች በአብላጫ ድምጽ ያልፋል፤

፬/ በኮሚሽኑ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ድምፅ እኩል ለእኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምፅ ወሳኝነት ይኖረዋል፤

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የኮሚሽኑ ምክር ቤት የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለ ኮሚሽነሮች</u>

**፲፩. <u>ስለኮሚሽነሮች</u>**

፩/ ኮሚሽኑ አሥራ አንድ (፲፩) ኮሚሽነሮች ይኖሩታል፤

፪/ የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር፤ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ሌሎች ኮሚሽነሮች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፤

፫/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሹመት ውሳኔውን የሚሰጠው የቀረቡት ዕጩዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ሥር የተቀመጡ መሥፈርቶችን ያሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ ይሆናል።

**፲፪. <u>የኮሚሽነሮች አሰያየም</u>**

የኮሚሽነሮች አሰያየም በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ጽህፈት ቤት ዕጩ የኮሚሽን አባላትን ከሕዝብ፣ ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከሲቪል ማኅበራት ኮሚሽነር ሊሆኑ የሚችሉ ግለሰቦችን ጥቆማ ይቀበላል፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ሥር በተቀመጡት መሥፈርቶች መሠረት ከተጠቆሙት ሰዎች ውስጥ ቢያንስ አስራ አራት ኮሚሽነር ሊሆኑ የሚችሉ ዕጩዎችን በመለየት የዕጩዎቹን ዝርዝር ለሕዝብ ይፋ በማድረግ፣ ለአፈ ጉባዔው ያቀርባል፤

፫/ የሚዘጋጀው የዕጩዎች ዝርዝር የፆታ እና ሌሎች የብዝሃነት መገለጫዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፤

፬/ አፈ ጉባዔው ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ አመራሮች እና ተወካዮች ጋር በቀረቡት ዕጩዎች ላይ ምክክር ያደርጋል፤

፭/ አፈ ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሥር የተገለፀውን ምክክር ካደረገ በኋላ ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል እንደየ አስፈሊጊነቱ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና ኮሚሽነር ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ዕጩዎችን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ያቀርባል።

**፲፫. <u>ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ መሥፈርቶች</u>**

ማንኛውም ኮሚሽነር ሆኖ የሚሾም ሰው የሚከተሉትን መሥፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

፩/ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤

፪/ ሁሉንም ሃይማኖቶች፣ የኢትዮጵያ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችን እና ሕዝቦችን በእኩል ዓይን የሚያገለግል፤

፫/ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፤

፬/ ለሀገራዊ መግባባት ጉልህ አስተዋፅዖ ሊያበረክት የሚችል፤

፭/ መልካም ሥነ-ምግባርና ስብዕና ያለው፤

፮/ በሕዝብ ዘንድ ዓመኔታ ያለው፣

፯/ በከባድ ወንጀል ተከሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ያልተላለፈት፤

፰/ የኮሚሽኑን ሥራ በአግባቡ ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ብቃት ያለው፤

፱/ ሙሉ ጊዜውን ለኮሚሽኑ ሥራ ለማዋል ፍቃደኛ የሆነ።

**፲፬. <u>የኮሚሽነሮች ደመወዝና ጥቅማጥቅም</u>**

የኮሚሽነሮች ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ለመንግሥት ከፍተኛ ተሿሚዎች በተፈቀደው ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም አግባብ ይፈፀማል።

## ፲፩. የኮሚሽነሮች መብትና ግዴታ

፩/ ማንኛውም ኮሚሽነር የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ያለመከሰስ መብቱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ካልተነሳ ወይም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር በኮሚሽነርነት በሚያገለግልበት ወቅት በወንጀል ያለመከሰስ መብት አለው፤

ለ) በኮሚሽኑ ምክር ቤት ሥራ ላይ በነፃነት የመሳተፍና ድምፅ የመስጠት፤

ሐ) ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን የማግኘት እና የመመልከት፤ እና

መ) የኮሚሽኑ ምክር ቤት በሚወስነው አግባብ የኮሚቴ ሥራዎች እና ሌሎች ሥራዎች ላይ የመሳተፍ።

፪/ ማንኛውም ኮሚሽነር የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) የኮሚሽኑን ተግባር እና ኃላፊነት በተገቢ ሁኔታ መፈፀም፤

ለ) ሙሉ ጊዜውን ለኮለሚሽኑ ሥራ የማዋል፤

ሐ) የጥቅም ግጭትን የማስወገድ፤

መ)በሥራ ሂደት ያገኘውን ምስጢር የመጠበቅ፤

ሠ) የኮሚሽኑን ገለልተኝነት መልካም ስም እና ክብር ከሚያጎደፍ እና ውጤታማነትን ከሚያደናቅፍ ድርጊት የመቆጠብ፤

ረ) ሌሎች የኮሚሽኑን ሥርዓቶች እና ደንቦች የማክበር።

## ፲፪. ኮሚሽነሮች ከኃላፊነት ስለሚነሱበት ሁኔታ

፩/ ማንኛውም ኮሚሽነር በሚከተሉት ሁኔታዎች ከኃላፊነት ሊነሳ ይችላል፡-

ሀ) በህመም ምክንያት መደበኛ ተግባሩን ማከናወን ባለመቻል፤

ለ) ግልፅ የሆነ የብቃት ማነስ ከታየበት፤

ሐ) ከባድ የሥነ-ምግባር ጉድለት ከታየበት፤

መ)ያለበቂ ምክንያት ለተከታታይ አስር ቀናት በሥራ ገበታው ላይ ካልተገኘ፤ ወይም

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ሥር ከተመለከቱት መስፈርቶች ውስጥ በሹመት ወቅት ኮሚሽነሩ ያላሟላው መሥፈርት መኖሩ ከተረጋገጠ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ኮሚሽነር ከኃላፊነት የሚነሳው ማንኛውም ማስረጃ ባለው ወገን ጠያቂነት የቀረበ ማመልከቻ አሳማኝ ነው ብሎ አፈ ጉባዔው ተቀብሎ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያስተላልፈው ጥያቄ ወይም ከአንድ ሶስተኛ በማያንሱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት አነሳሽነት ወይም ከሦስት በማያንሱ ኮሚሽነሮች ጥያቄ መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያስተላልፈው ውሳኔ ይሆናል።

## ፲፫. ኃላፊነትን በገዛ ፍቃድ ስለመልቀቅ

ማንኛውም ኃላፊነቱን በገዛ ፍቃዱ መልቀቅ የሚፈልግ ኮሚሽነር የሁለት ወር የጽሁፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለኮሚሽነሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ በመስጠት ሊለቅ ይችላል።

## ፲፰. ስለሌላ መንግስታዊ ኃላፊነት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ከኃላፊነት የተነሳ ወይም በአንቀጽ ፲፯ መሠረት በገዛ ፍቃዱ ከኃላፊነት የለቀቀ ኮሚሽነር ለሁለት ዓመት ለሌላ የመንግስታዊ ኃላፊነት አይታጭም።

## ፲፱. ኮሚሽነር ስለመተካት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ እና ፲፯ መሠረት ኮሚሽነር ከኃላፊነት ሲነሳ ወይም ሲለቅ ወይም በሞት ምክንያት ሲለይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ለአፈ ጉባዔው ከተላኩለት የዕጩዎች ዝርዝር መካከል በኮሚሽነርነት ካልተሾሙት ዕጩዎች ውስጥ ተተኪ ኮሚሽነር ሆኖ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾም ያደርጋል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከኃላፊነት የተነሳ ወይም የለቀቀ ወይም በሞት ምክንያት የተለየው ዋና ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ዋና ኮሚሽነሩ በሆነ ጊዜ ከተሾሙ ኮሚሽነሮች ወይም ከተጠባባቂ ዕጩ ኮሚሽነሮች መካከል በመምረጥ እንዲሾሙ አፈ ጉባዔው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል።

# ክፍል አራት

# ስለኮሚሽኑ ምክር ቤት፤ ዋና ኮሚሽነር እና ጽህፈት ቤት

## ፳. የኮሚሽኑ ምክር ቤት

የኮሚሽኑ ምክር ቤት ሁሉንም ኮሚሽነሮች በአባልነት ያቀፈ ነው።

## ፳፩. የኮሚሽኑ ምክር ቤት ተግባር እና ሥልጣን

የኮሚሽኑ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የሕዝብ ምክክር የሚደረግባቸውን አጀንዳዎች በዝርዝር በመፈተሽ ምክክር እንዲደረግባቸው መወሰን፤

፪/ በኮሚቴዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ እና በሕዝባዊ ውይይቶች የተገኙ ምክረ ሃሳቦችን በዝርዝር በመፈተሽ እና በማጠናቀር ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለአስፈፃሚ አካሉና ሌሎች የሚመለከታቸዉ የመንግሥት አካላት እንዲቀርብ ማፅደቅ፤

፫/ የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና ዕቅድ መርምሮ የማፅደቅ፤

፬/ የጽህፈት ቤቱን አጠቃላይ ሪፖርት መርምሮ የማፅደቅ፤

፭/ አስፈላጊ ኮሚቴዎችን የማቋቋም፤

፮/ በክልሎች የጽህፈት ቤቱን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እንዲቋቋሙ የመወሰን፤

፯/ የጽህፈት ቤቱን የኦዲት ግኝት መርምሮ የማፅደቅ፤

፰/ የምክር ቤቱ ዋና ኮሚሽነርና ምክትል ዋና ኮሚሽነር በተመሳሳይ ጊዜ በሥራ ገበታቸው ላይ ለተከታታይ አስር ቀናት ካልተገኙ ከአባላቶቹ መካከል ጊዜያዊ ሰብሳቢ የመምረጥ፤

፱/ የጽህፈት ቤቱን መዋቅራዊ አደረጃጀት የማፅደቅ፤

፲/ የጽህፈት ቤቱን ኃላፊ ሹመት የማፅደቅ፤

፲፩/ አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት፤

፲፪/ የኮሚሽነሮች የሥነ ምግባር መመሪያ የማውጣት፤

፲፫/ የጽህፈት ቤቱን መተዳደሪያ ደንብ የማውጣት፤

## ፳፪. የዋና ኮሚሽነር ተግባር እና ሥልጣን

የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር የሚከተሉት ተግባር እና ሥልጣን ይኖሩታል፡-

፩/ የኮሚሽኑን ምክር ቤት በሰብሳቢነት ይመራል፤

፪/ አጠቃላይ የኮሚሽኑን ሥራ የመምራት፤

፫/ የኮሚሽኑን ምክር ቤት ስብሰባ አጀንዳዎችን የማቅረብ፤

፬/ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት፤

፭/ የጽህፈት ቤቱን አጠቃላይ ሥራ የመቆጣጠር፤

፮/ ኮሚሽኑን በመወከል ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት የማድረግ፤

፯/ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርቶችን የማቅረብ፤

፰/ የኮሚሽኑን የጽህፈት ቤት ኃላፊ ዕጩ ለምክር ቤት አቅርቦ የማሾም፤

፱/ የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌደራል መንግስት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የመቅጠር እና የማስተዳደር፤

፲/ የኮሚሽኑን በጀት ጥያቄ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በማዘጋጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ፤

፲፩/ ሌሎች በኮሚሽኑ ምክር ቤት የሚሰጡትን ተግባራት የማከናወን።

## ፳፫. የምክትል ዋና ኮሚሽነር ተግባር እና ሥልጣን

የኮሚሽኑ ምክትል ዋና ኮሚሽነር የሚከተሉት ተግባር እና ሥልጣን ይኖሩታል፡-

፩/ ዋናው ኮሚሽነር በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

፪/ በዋናው ኮሚሽነር የሚሰጡትን ተግባራት ይፈጽማል።

## ፳፬. ስለኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት

፩/ የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት ኮሚሽነር ባልሆነ ኃላፊ ይመራል።

፪/ ጽህፈት ቤቱ ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

፫/ ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለዋናው ኮሚሽነር ይሆናል።

## ፳፭. የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት ተግባር እና ኃላፊነት

የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ተግባር እና ሥልጣን ይኖሩታል፡-

፩/ የኮሚሽኑን ጽህፈት ቤት መዋቅራዊ አደረጃጀት ለይቶ ለኮሚሽኑ ምክር ቤት አቅርቦ የማፀደቅ፤

፪/ ለኮሚሽኑ አጠቃላይ የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት የመስጠት፤

፫/ ለኮሚሽኑ ተግባር እና ኃላፊነት አስፈላጊ የሆኑትን ግብዓቶችን እና ሌሎች አገልግሎቶችን የማቅረብ፤

፬/ የኮሚሽኑን ቃለ ጉባዔዎች፣ ውሳኔዎች፣ የሂሳብ መዛግብት እና ሌሎች መረጃዎችን በሚገባ አደራጅቶ የመያዝ፤

፭/ የኮሚሽኑን በጀት በማዘጋጀት ዋና ኮሚሽነሩን ማገዝ፤ እና

፮/ ሌሎች በምክር ቤቱ ወይም በዋና ኮሚሽነሩ የሚሰጡትን ተግባራት ማከናወን።

## ፳፮. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ተግባር እና ኃላፊነት

፩/ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ተግባር እና ሥልጣን ይኖሩታል፡-

ሀ) የጽህፈት ቤቱን መዋቅራዊ አደረጃጀት ለይቶ ለኮሚሽኑ ምክር ቤት አቅርቦ የማፀደቅ፤

ለ) የጽህፈት ቤቱን ተግባራት አስመልክቶ ለዋናው ኮሚሽነር እና ለኮሚሽነሮች ምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ፤

ሐ) የጽህፈት ቤቱን የሥራ ዕቅድ ለኮሚሽኑ ምክር ቤት አቅርቦ የማፀደቅ፤ እና

መ) በዚህ አዋጅ ለጽህፈት ቤቱ የተሰጡትን ተግባራት እና ሥልጣን በመምራት የማስተዳደር።

፪/ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነት ለኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ይሆናል።

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፳፯. የበጀት ምንጭ

፩/ የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌሎች ሕጋዊ ምንጮች ማግኘት ይችላል።

፫/ የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በኮሚሽኑ ምክር ቤት በሚፀድቅ የውስጥ ደንብ መሠረት ኮሚሽኑ በጀቱን የማስተዳደር ሙሉ ነፃነት አለው።

**፳፰. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

፩/ ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**፳፱. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኮሚሽነሮችን፣ የኮሚሽኑን ሠራተኞች፣ አወያዮችና በውይይት ሂደቱ የሚሳተፉ አካላትን የሥነ-ምግባር ሁኔታ በተመለከተ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፪/ የኮሚሽነሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፴. <u>ስለ ኮሚሽኑ ሰነዶች</u>**

፩/ ኮሚሽኑ የሥራ ጊዜው ሲያበቃ በኮሚሽኑ የሥራ ዘመን በተካሄዱ ሀገራዊ ምክክሮች ወቅት የተዘጋጁ ሰነዶች፣ የተያዙ ቃለ-ጉባዔዎችና መሰል ሰነዶች ተጠብቀዉ እንዲቆዩ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት እንዲሁም ለኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መፃህፍት አገልግሎት የማስረከብ ኃላፊነት አለበት።

፪/ የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መፃህፍት አገልግሎትም ከኮሚሽኑ የተቀበላቸውን ሰነዶች በአግባቡ አደራጅቶ የማስቀመጥና ለተለያየ ዓላማ ማየትና መጠቀም ለሚፈልጉ ሰዎች መጠቀም እንዲችሉ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

**፴፩. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚያቀርበው ማንኛውም ሕጋዊ ጥያቄ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት።

**፴፪. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

**፴፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከታህሳስ ፳ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ. ም**

**ሳህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**PROCLAMATION No.1265/2021**

**A PROCLAMATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN NATIONAL DIALOGUE COMMISSION**

**Addis Ababa/Ethiopia**

**2023**

**WHEREAS,** there are difference of opinions and disagreements among various political and opinion leaders and also segments of society in Ethiopia on the most fundamental national issues and it is a necessity to resolve the differences and disagreements through broad based inclusive public dialogue that engenders national consensus;

**WHEREAS,** enormously conducting inclusive National Dialogues is important to bolster national consensus along the way a culture of trust and of working together as well as mend degraded to restore social values; the National Dialogue process societal values and since it has become necessary to legally institute a system that facilitates the National Dialogue process;

**WHEREAS,** the legitimacy and credibility of National Dialogue processes is contingent upon among others the capability and impartiality of the entity that facilitates and leads the deliberations and since it has become necessary to establish an institution with widespread legitimacy that could coordinate and lead the deliberations capably and impartially;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "The Ethiopian National Dialogue Commission Establishment Proclamation No. 1265 /2021"

**2. Definition**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ **"The Council of the Commission"** means a Council constituted by all the Commissioners of the National Dialogue Commission;

2/ **"Comissioner"** means the Commissioner of the National Dialogue Commission appointed by the House of Peoples' Representatives, based upon nomination by the Speaker in accordance with Article 12 of this Proclamation;

3/ **"National Dialogue"** means consultation of different bodies facilitated by the Council of Commissions at the Federal and Regional level on the Agendas identify in accordance with this Proclamation and the Directives to be issued by the Council of Commissions;

4/ **"Region"** means any Region established as per Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

5/ **"Panellist"** means a person who appointed by the Council of Commissions to lead National Dialogue forums held in Federal and Regional level;

6/ **"Person"** means any natural person or juridicial person;

7/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Principles of the National Dialogue**

1. The National Dialogue and the general works of the Commission shall be directed by the following principles:
   a) inclusivity;
   b) transparency;
   c) credibility;
   d) tolerance and mutual respect;
   e) rationality;
   f) implementation and context sensitivity;
   g) impartial facilitator;
   h) depth and relevance of Agendas;
   i) democracy and rule of law;
   j) national interest;
   k) using national traditional knowledge and values.

2/ The Council of the Commission may include additional principles it deems necessary.

## PART TWO
## ESTABLISHMENT OF THE COMMISSION, OBJECTIVE, STRUCTURE, DUTIES AND RESPONSIBILITIES

**4. Establishment**

1/ The Ethiopian National Dialogue Commission (hereinafter "the Commission"), an impartial and independent organ of the Federal Government with its own legal personality has been hereby established by this Proclamation.

2/ The Commission shall be accountable to the House of Peoples' Representatives.

**5. Head Quarter**

The head quarters of the Commission shall be in Addis Ababa and it may have branch offices in Regional States as necessary.

**6. Objectives of the Commission**

The Commission shall have the following objectives:

1/ Facilitate consultation between the various segments of the society by identifying the root causes of the difference on fundamental national issues and identifying the topics on which the discussion will take place;

2/ Implement an effective National Dialogue process by ensuring that National Dialogues are inclusive, lead by a competent and impartial body, with a clear focus on the cause of disagreements, guided by transparent system, and have a plan to implement the results of the consultations;

3/ Establish a system of deliberations that will improve the relationship among the different segments of the population as well as between the public and the Government so as to enable the creation of new political dispensation that is marked by mutual trust;

4/ Support the implementation of the recommendations made by the dialogues and build a democratic system of trust between citizens, the government and the People at the national level;

5/ To develop a political culture that can solve internal problems that have been simmering for centuries through dialogues and create a conducive environment for the building of a democratic system;

6/ Lay the social and political foundations on the basis of which current problems can be solved in a sustainable manner, ensuring lasting peace;

7/ Lay a firm foundation for national consensus and the building of a State with strong legiti- macy.

**7. <u>Organization</u>**

The Commission shall have:

1/ A Council of Commissioners;

2/ A chief Commissioner;

3/ A deputy chief Commissioner;

4/ A Secretariat;

5/ Committees as may be necessary and

6/ Necessary staff.

**8. <u>Term of the Commission</u>**

1/ The term of the Commission shall be three (3) years.

2/ If necessary, the term of the Commission may be extended by the House of Peoples' Representatives.

3/ The term of the Commission shall commence from the time Commissioners have been appointed in accordance with this Proclamation.

**9. <u>Duties and Responsibilities of the Commission</u>**

The Commission shall have the following duties and responsibilities:

1/ It shall establish Committees and teams of experts that will facilitate and implement dialogues, conduct studies and generate recommendations;

2/ It shall study national dialogue processes that had been carried out by governmental or non-governmental entities and their outcomes, and shall use the same as input in national deliberations it will conduct;

3/ It shall identify differences among different political and opinion leaders and also between societies on national issues through studies, public discussions or other appropriate modalities;

4/ Craft agenda for dialogue, based on issues identified in accordance with Sub-Article (3) of this Article organize dialogues and facilitate deliberations;

5/ It shall organize and convene dialogue forums at the Federal and Regional levels that would bring about national consensus with the participation of representatives of various segments of society drawn from the entire country;

6/ It shall identify and enable participants to take part at a national dialogue conference in accordance with clear criteria, issued detail Directive on this matter;

7/ It shall cause dialogues to be chaired by com missioners or facilitators to be appointed by the Council of Commission, it ensures that the person who are appointed as facilitators meet the qualifications for Commissioner as provides under Article 13 of this Proclamation as much as possible;

8/ It shall appoint professionals who will take minutes of dialogues, consolidate and organize the recommendations of the dialogues and present the same to the Council of Commission;

9/ It shall enact and implement internal Regulations and Directives pertaining to the secretariat internal working procedures, the selection of topics or Agenda for the dialogue and selection of participants to take part in National Dialogue forums;

10/ Prepare a document for the National Dialogue Conference Agendas, the process of the dialogues, the recommendations obtained from the dialogues and strategies to implement the recommendations, and submit the same to the House of Peoples' Representatives, to the Executive organ and to the relevant organs, and also disclose to the public;

11/ Provide support to the government in the preparation of a clear and concrete plan that would enable it to implement the recommendations arising out of the national dialogue;

12/ It shall devise a system to monitor the implementation of recommendations;

13/ It shall carry out other activities necessary to accomplish its objectives.

**10. <u>Meeting of the Council of the Commission</u>**

1/ The regular meetings of the Commission shall be held in accordance with the internal rules of procedure of the Council of the Commission. However, the Council of the Commission may hold extraordinary meetings when such meetings are called by the Chief Commissioner or at the request of fifty plus one (50+1) of the Commissioners;

2/ The quorum of the Council of the Commission is constituted if fifty plus one (50+1) of the Commissioners are present;

3/ The decisions of the Commission shall be held by agreement of the members of the Council of the Commission; However, if no agreement is reached the decisions shall be passed by a majority vote of Commissioners present;

4/ In the event of a tie, the chair of the meeting shall have the casting vote;

5/ without prejudice to the provisions of this Article, the Commission may adopt its own rules of procedure for its own meetings.

## PART THREE
## THE COMMISSIONERS

### 11. The Commissioners

1/ The Commission shall have eleven (11) Commissioners;

2/ The Chief Commissioner of the Commission, the Deputy Chief Commissioner and other Commissioners shall be appointed by the House of Peoples' Representatives;

3/ The House of Peoples' Representatives shall decide on the appointment of the nominees after ascertaining that they fulfil the criteria set out under Article 13 of this Proclamation.

### 12. Appointment of Commissioners

Commissioners shall be appointed in the following manner:

1/ The Secretariat of the Speaker of the House of Peoples' Representatives shall receive from the public, political parties and civil society nominations of individuals who could serve as Commissioners;

2/ In accordance with the requirements set out in Article 13 of this Proclamation, the office of the Speaker of the House of Peoples' Representatives shall prepare a shortlist of at least fourteen potential candidates for the post of Commissioner, disclose to the public and submit it to the the Speaker of the House of Peoples' Representatives;

3/ The list of candidates shall be inclusive of gender and other forms of diversity;

4/ The Speaker shall consult with the leadership and representatives of opposition political parties, civil society organizations and the interreligious Council on the list of nominees.

5/ After conducting the consultation provided for under Sub-Article (4) of this Article, the Speaker shall submit to the House of Peoples' Representatives nominations for appointments to the post of Chief Commissioner, Deputy Chief Commissioner and Commissioners.

### 13. Criteria for the Appointment of Commissioners

Anyone who shall be appointed as a Commissioner shall fulfil the following requirements:

1/ Ethiopian National;

2/ Committed to serve all religions, Nations, Nationalities and Peoples of Ethiopia equally;

3/ Not a member of any political party;

4/ Capable to make a significant contribution to national consensus;

5/ Have a good character and personality;

6/ Trust worthy by the public;

7/ Not convicted for charges of committing any serious crime;

8/ Shall have a competence to discharge the activities of the commission;

9/ Willing to devote his full time for the activities of the Commission.

### 14. Renumeration and Benefits of Commissioners

The renumeration and benefits of the Commissioners shall be provided in accordance with the benefits and salary scheme of Senior Government Officials.

### 15. Obligations and Rights of Commissioners

1/ Any Commissioner shall have the following rights:

a) unless he is caught in flagrante delicto or his immunity is stripped by the House of Peoples' Representatives, shall have immunity from criminal prosecution during the course of his service as a Commissioner;

b) freely participate and vote in the work of the Council of the Commission;

c) get access to and consult documents and other information useful for the work of the Commission; and

d) participate in committees and other works of the Commission in accordance with the decision of the Council of the Commission.

2/ Any Commissioner shall have the following obligations:

a) discharge the responsibilities and duties of the Commission with due care;

b) devote his full time to the work of the Commission;

c) avoid conflict of interest;

d) maintain the confidentiality of secrets acquired in the course of his work;

e) refrain from engaging in conduct that could undermine the Commission's impartiality, reputation, prestige and impede its effectiveness;

f) respect any other rules and Regulations of the Commission.

### 16. Removal of Commissioners

1/ Any Commissioner could be removed from his position on any of these grounds:

a) If he is incapable of discharging his responsibility due to serious illness;

b) If he is manifestly incompetent;

c) If he engages in serious misconduct;

d) If he fails to be present at his post of duty consecutively for ten days without sufficient justification; or

e) If it is found that he had not fulfilled one of the requirements provided under Article 13 of this Proclamation during his appointment.

2/ A Commissioner shall be removed from his post by a decision of the House of Peoples' Representatives when a request for such removal is submitted to the Speaker of the House by anyone with evidence of the existence of one of the grounds stipulated under Sub-Article (1) of this Article and if the request is deemed credible by the Speaker and is tabled for the decision of the House, or a request for removal is initiated by one third member of the House or not less than three Commissioners, and a decision in favor of the removal is passed by the House of Peoples' Representatives.

**17. Resignation**

Any Commissioner who desires to resign from the Commissions could do so after providing a two-month prior written notice to the Council of the Comission and the Speaker of the House of Peoples' Representatives.

**18. Other Government Post**

Any Commissioner who is removed from his post pursuant to Article 16 or resign voluntarily pursuant to Article 17 shall not be nominated for other Government post for two years.

**19. Replacement of a Commissioner**

1/ A Commissioner shall be appointed by the House of Peoples' Representatives among the list of candidates who are not appointed as provided under Article 12 of the Proclamation where a Commissioner is removed or resigns, or dies Pursuant to Article 16 and 17 of this Proclamation.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Speaker shall present for the House of Peoples' Representatives for appointment from the appointed Commissioners or from nominated candidate Commissioners where a Commissioner removed or resigns, or dies is Chief Commissioner or Deputy Chief Commissioner.

## PART FOUR

## COUNCIL OF THE COMMISSION, CHIEF COMMISSIONER AND SECRETARIAT

**20. Council of the Commission**

The Council of the Commission shall constitute all Commissioners.

**21. Powers and Responsibilities of the Council of the Commission**

The Council of the Commission shall have the following powers and responsibilities:

1/ Examine potential topics for public dialogue and set the Agenda for public deliberation;

2/ Examine and compile detail recommendations that have been prepared by Committees and generated in public dialogue forums and adopt to be submitted to the House of Peoples' Representatives, the Executive organ and other relevant government organs;

3/ Examine and adopt the annual budget of the secretariat;

4/ Examine and adopt the overall report of the secretariat;

5/ Establish necessary Committees;

6/ Decide to establish branch offices in Regional states;

7/ Examine and adopt the audit report of the secretariat;

8/ Elect a temporary chairperson among its members of the Chief and Deputy Chief Commissioners are absent from their post for a consecutive period of ten days;

9/ Adopt the organizational structure of the Secretariat;

10/ Approve the appointment of the Head of the Secretariat;

11/ Issue Directives necessary to implement the Proclamation;

12/ Adopt the Commissions' Code of Conduct;

13/ Adopt the internal Regulation of the Secretariat.

**22. Responsibilities and Powers of the Chief Commissioner**

The Chief Commissioner shall have the following responsibilities and powers:

1/ He shall serve as the chairperson of the Council of the Commission;

2/ Lead the overall activities of the Commission;

3/ Table the Agenda of the Council of the Commission;

4/ Call extraordinary meetings of the Council of the Commission as necessary;

5/ Oversee the overall activity of the secretariat;

6/ Represent the Commission in its relationship with other organs;

7/ Present a report to the House of Peoples' Representatives;

8/ Present to the Council of the Commission a nominee to be appointed as Head of the Secretariat;

9/ Hire and administer the staff of the Commission in accordance with Federal Civil Servants Law;

10/ Prepare the budget of the Commission jointly with the Ministry of Finance and present the same to the House of Peoples' Representatives for approval;

11/ Carry out other tasks assigned to him by the Council of the Commission.

**23. Responsibilities and Powers of the Deputy Chief Commissioner**

The Deputy Chief Commissioner shall have the following responsibilities and powers:

1/ Carry out the duties of the Chief Commissioner in his absence;

2/ Perform tasks assigned to him by the Chief Commissioner.

**24. Secretariat of the Commission**

a) The Secretariat of the Commission shall be lead by a head who is not a Commissioner.

b) The Secretariat shall have other necessary staff.

c) The Secretariat shall be accountable to the Chief Commissioner.

**25. The Responsibilities and Duties of the Secretariat of the Commission**

The Secretariat of the Commission shall have the following responsibilities and powers:

1/ Identify the organizational structure of the office of the Commission for the approval to the Council of the Commission;

2/ Provide overall administrative and financial services to the Commission

3/ Provide the inputs and other services necessary for the performance of the activities and responsibilities of the Commission;

4/ Keep the minutes, records of the decisions, financial documents and other information in an organized manner;

5/ Assist the Chief Commissioner in the preparation of the budget of the Commission; and

6/ Perform other responsibilities to be assigned to it by the Council of the Commission or the Chief Commissioner.

**26. Responsibilities and Duties of the Head of the Secretariat of the Council**

1/ The Head of the Secretariat shall have the following duties and responsibilities:

a) prepare the organizational structure of the Commission to the Council for its approval;

b) provide a report regarding the activities of the Secretariat to the Chief Commissioner and the Council of the Commission;

c) present the work plan of the Secretariat to the Council of the Commission for approval; and

d) lead and administer the Secretariat in the performance of the duties and responsibilities assigned to it in this Proclamation.

2/ The Head of the Secretariat shall be accountable to the chief Commissioner.

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**27. Source of the Budget**

1/ The budget of the Commission shall be allocated by Government.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Commission may collect fund from other legal sources.

3/ The Commission has the full power to administer its budget independently in accordance with the Principles of government finance administration through internal bylaw to be adopted by the Council of the Commission.

**28. Books of Accounts**

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Commission shall be audited annually by the Auditor General or by Auditors designated by him.

**29. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The House of Peoples' Representatives may issue Regulation regarding the discipline conditions of Commissioners, Employees of Commission, panellists and Organs take part in the consultation process.

2/ The Council of the Commission may issue Directives necessary for the effective implementation of this Proclamation and Regulations issued under Sub-Article (1) of this Article.

**30. Documents of the Commission**

1/ The Commission shall have a responsibility to handover, the documents prepared in time of national dialogue, minutes and other similar documents prepared in the term of the Commission, to the Secrteriat of the House of Peoples' Representatives and to the Ethiopian Archives and Library Service for preservation.

2/ The Ethiopian Archives and Library Service shall have the responsibility, the received documents, to properly organize, preserve and produce conditions for person who wants to see and use the documents for different purpose.

**31. Duty to Cooperate**

Everyone has an obligation to cooperate with the Commission pursuant to any lawful request of the Commission in the discharge of its mandate.

**32. Inapplicable Laws**

No laws, in so far that they are inconsistent with this Proclamation, shall be applicable with respect to matters covered under this Proclamation.

**33. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force upon the date its approval by the House of Peoples' Representatives on the 29th day of December 2021.

**Done at Addis Ababa, on this, 13th Day Of January, 2022**

**SAHLE WORK ZEWEDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**